## *በጌታ ፀጋና ዕውቀት ማደግ*

<u>የትምህርቱ ዋና ጥቅስ፡</u>

**2ጴጥ3፡18** "ነገር ግን በጌታችን በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ዕውቀት እደጉ …"

- በዚህ ስፍራ በእግዚአብሔር ነገር የሸመገለው ሐዋርያ ጴጥሮስ መልክቱን ለፀፈላቸው ክርስትያኖች የመጨረሻ ምክር የሰጠቸው ቃል ነው።
- ሐዋርያ ጴጥሮስ ይህንን መልዕክት የፀፈው ለማን ነው? (2ጴጥ3፡1 ፣ 1ጴጥ1፡1-2)
- ይህን መልዕክት ሐዋርያ ጴጥሮስ የፀፈበት ምክንያቱ ምንድነው?
    - የሱ መሞት የተቀረበና የማይቀር መሆኑን (2ጴጥ1፡14)
    - ሀሰተኛ አስተማሪዎች እነሱን ለማሳሳት እንደሚነሱ (2ጴጥ2፡1-2)
    - እንድነቃቁና የጌታን ትዕዛዛት እንድጠብቁ ነው።(2ጴጥ3፡1-2)
- ስለዚህ መልዕክቱ ልብን የሚነካ የሐዋርያ ጴጥሮስ የመጨረሻ ምክር ነው።
    1. ሐዋርያ ጴጥሮስ በጌታ ፀጋና ዕውቀት ዕደጉ ስል ምን ማለቱ ነው?
    2. ለክርስትያ ሁሉ የሚያስፈልጉ እነዚህ ፀጋዎችስ ምንደናቸው?
    3. በጌታ ፀጋና ዕውቀት ለማደግ ለምን ያስፈልጋል?
    4. አንድ ክርስትያን በጌታ ፀጋና ዕውቀት ለማደግ እንዴት ይችላል? ማደጉንስ በምን ያውቃል?

I. <u>በጌታ ፀጋና ዕውቀት ማደግ ምንድነው?</u>

ሀ. ስምንቱን የፀጋ ስጦታዎች በህይወታችን ማሳደግ ማለት ነው።በ2ጴጥ1፡5-7




2ጴጥ1፡8 - እነዚህ ባህርያት "ተትረፍርፈው" ቢኖራችሁ

ለ. እነዚህን ፀጋዎች በህይወታችን በአንድነት ማሳደግ አለብን። - መጨመሪ የሚለውን ቃል ተመልከት (2ጴጥ1፡5)

ሐ. ፀጋዎቹ በህይወታችን እንድያድጉ መትጋት አለብን። (2ጴጥ1፡5፣ 2ጴጥ1፡10)

II. <u>ጌታን አሁን ከምናውቀው በላይ ማወቅ ለምን ያስፈልጋል?</u>

1. ጌታ በማወቅ በደግን ቁጥር የእግዚአብሔር ፀጋና ሰላም ይበዛልናል። (2ጴጥ1፡2)
2. ጌታን በማወቅ "ለህይወትና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት" የሚያስፈልገንን ሁሉ በመለኮታዊ ሀይል እናገኛለን። (2ጴጥ1፡3)
3. ጌታን በሚገባ በማወቅ ከመንፈሳዊ አሰተሳሰብ ጠባብነት (የሩቁን የለማየት) እና ዕውርነት እናስወግዳለን።(2ጴጥ1፡9)
    - የክርስቲያኖች የመጨረሻው ግብ - ክርስቶስን መምሰል ነው። (ሮሜ8፡29፣ ቆላ3፡9-11)-
4. በጌታ ዕውቀት ከደግን በህይወታችን እንዳንሰናከል ይረዳናል። (2ጴጥ1፡10)
5. በጌታ ዕውቀት ከደግን - ወደ ዘላለማዊ ህይወት በሙላት እንገባለን። (2ጴጥ1፡11)